**Kinijit International Council**

**ቅንጅት ዓለምአቀፍ ላዕላይ ምክርቤት**

P. O. Box 10441 Marina Del Rey CA 90295 USA

# የሠላምና የዴሞክራሲ ትግል በሴረኞች እኩይ ተግባር አቅጣጫውን አይለውጥም!!

ቅንጅት ለአንድነትና ዴሞክራሲ ከፅንሰ መሠረቱ አንደኛና የመጀመሪያ ዓላማና ግብ አድርጎ የተነሳበት መርህ ሰላምና ዴሞክራሲ መሆኑን በማኒፌስቶውም ሆነ በተለያየ ጊዜና ሁኔታ ሳያስገነዝብ ያለፈበት ጊዜ የለም።

ነገር ግን አንዳንድ ቡድኖች ከቅንጅት ጋር የተጣመሩና ድርጅቱ በእነርሱ የትግል መስመር ውስጥ እንዳለ እያስመሰሉ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሀንና መጣጥፎች እያቀረቡ ነው።

ለኢትዮጵያ ሕዝብና በአገራችን ዴሞክራሲ መምጣት ለሚመኙና ለሚታገሉ ሁሉ ደግመን ደጋግመን የምናሳስበው የቅንጅት የትግል መርህ ሠላምን ብቻ የሚከተል መሆኑን ነው።

አንዳንዶቹም ከቅንጅት ተገንጥለው ከሄዱ በኋላ በሌላ መስመር ሊታገሉ ሲሞክሩ የቅንጅትን ሊቀመንበር በእነርሱ የተገንጣይ መስመር እንደገቡ አስመስለው በልዩ ልዩ መገናኛ ብዙሀን ሲገልጹ ሰምተናል።

የአንድነት ጎራ የተገንጣይ ጎራ ሆኖ እንደማያውቅ ሁሉ ዛሬ የቅንጅት መሪ ከተገንጣዮች ጋር እንደሚተባበሩ አድርገው የሚያሰሙት አሉባልታ ሕዝብን ለማሳሳት በመሆኑ ይህን ጉዳይ ተገንዝቦ ሕዝቡ እንዳይቀበላቸው እናሳስባለን።

ለወደፊትም በዚህ አካሄድ ሐሰት እንዳይሰራጭና የትግሉ ጉዞ እንዳይደናቀፍና አባሎችና ደጋፊዎች የቅንጅትን የማይቀለበስ ሰላማዊ የትግል መስመር ይዘው እንዲታገሉ እናሳስባለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰላማዊ መንገድ ታግሎ ነፃነቱን ያረጋግጣል!!

መጋቢት 2008ዓ.ም.(እ.ኤ.አ)

ቅንጅት ዓለምአቀፍ ምክር ቤት